የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሣኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No 1
ADDIS ABABA,8th November, 2023

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፵፩/፪ሺ፲፮

የብሔራዊ የተሐድሶ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ ደንብ…………………ገጽ ፲፭ሺ፪፻፵፪

**Content**

Regulation No. 541/2023

Regulation for the Amendment of National Tehadso Commission Establishment Regulation…………………….............Page 15242

**ደንብ ቁጥር ፭፻፵፩/፪ሺ፲፮**

**የብሔራዊ የተሐድሶ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፩፻፫ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የብሔራዊ የተሐድሶ ኮሚሽን ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፵፩/፪ሺ፲፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ማሻሻያ**

የብሔራዊ የተህድሶ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፭፻፳፭/፪ሺ፲፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

**Regulation No 541/2023**

**REGULATION FOR THE AMENDMENT OF NATIONAL TEHADSO COMMISSION ESTABLISHMENT REGULATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 103 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as “The Establishment of National Tehadso Commission Amendment Council of Ministers Regulation No 541/2023”

2. **Amendment**

The establishment of The National Tehadso Commission Council of Ministers Regulation No. 525/2022 is hereby amended as follows:

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፫(፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፤

"(፪) የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለመከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል።"

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፮ (፲፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) ተተክቷል፤

"(፲፩) ኮሚሽኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም አስፈላጊ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በቦርዱ ያፀድቃል።"

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፯(፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

"(፩) ብሔራዊ የተሐድሶ ቦርድ(ከዚህ በኋላ"ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ)"

፬/ የደንቡ አንቀጽ ፱ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተተክቷል፤

፱. <u>የቦርድ አባላት</u>

፩/ ቦርዱ አግባብ ካላቸው አካላት የተውጣጡ አባላትን ያካተተ ይሆናል፤

፪/ የቦርዱ ሰብሳቢ እና የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ይሆናል፤

፫/ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፡፡"

፭/ በደንቡ አንቀጽ ፲ እና ፲፩ ድንጋጌዎች ስር "ምክር ቤት" የሚለው ሐረግ ተሰርዞ "ቦርድ" በሚለው ቃል ተተክቷል።

1) Article 3 (2) of the Regulation is deleted and the following new Sub Article (2) is added.

"(2) The Commission shall be accountable to the Ministry of Defense."

2) Article 6 (11) of the Regulation is deleted and the following new Sub Article (11) is added:

"(11) The Commission may initiate Directives necessary for the effective implementation of this Regulation to be approved by the Board."

3) Article 7 (1) of the Regulation is deleted and the following new Sub Article (1) is added.

"(1) the National Tehadso Board (hereinafter called "Board.")

4) Article 9 is hereby deleted and the following new Article 9 is added:

"9. **<u>Members of the Board</u>**

1/ The Board shall have members from relevant bodies;

2/ Members and the Chairperson of the Board shall be determined by the Prime Minister.

3/ The Commissioner of the Commission shall serve as Secretary of the Board."

5) The phrase "Council" under the provisions of Articles 10 and 11 of the Regulation is deleted and substituted by the word "Board."

**፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ አሊ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**3. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force up on the date of the ratification by the Council of Ministers.

**Done at Addis Ababa on this 8th Day of November, 2023.**

**ABIY AHMED ALI (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**